# የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የተቀናጀ የሰራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት

## integrated of civil service management information system ( ICMIS)

## ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለመገምገም የተዘጋጀ ኦዲት ሪፓርት

ሚያዚያ/2010

አዲስ አበባ

# Contents


ማጠቃለያ / Executive summary/ ........ I

ፕሮጀክቱ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት እና አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮለት ወደ ስራ መግባቱን በተማለከተ ........ II

ፕሮጀክቱ የሚሜራበት የአፈፃፀምመመሪያ መኖሩን በተማለከተ ........ II

የዕቃ፣ ግንባታና አገልግሎት ግዥ/ የጨረታ ሂደቱን በተማለከተ ........ III

የዳታ ማዕከሉን ግንባታ በተማለከተ ........ III

የበለፀገውን ሶፍትዌር በተሚጢቅ ማዕከሎች ማዘርጋትን (ሲስተሙ ማስፋፋትን) በተማለከተ ........ III

ድጋፍና ክትትል በተማለከተ ........ IV

ቋሚየ ግንኙነት መድረክ ስለመኖሩ በተማለከተ ........ IV

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ I

የፕሮጀክቱ ደሰሳ ........ 2

የፕሮጀክቱ አስፈላጊነት/Rationale/ ........ 2

የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ........ 3

የፕሮጀክቱ ዓላማ ........ 3

የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ተግባራት ........ 5

የፕሮጀክቱ ወሰን ........ 6

የፕሮጀክቱ ውጤት ........ 6

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰውኃይል ........ 7

የፕሮጀክቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 7

የፕሮጀክቱ ስጋቶች(Project Risks) ........ 8

የኦዲቱ ዓላማ ........ 9

ለኦዲቱ የተሚጢው የኦዲቱ አካባቢ ........ 10

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) እና መመዘኛ ማስፈርቶች ........ 10

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 11

የስራ ሂደት መግለጫ(process description) ........ 13

ክፍል ሁለት ........ 14

ግኝቶች ........ 14

አደረጃጀትንና መሚያዎችን በተማለከተ ........ 14

ፕሮጀክቱ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት እና አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮለት ወደ ስራ መግባቱን በተማለከተ ........ 14

ፕሮጀክቱ የሚሜራበት የአፈፃፀምመመሪያ መኖሩን በተማለከተ ........ 15

የተገልጋይ ማንዋል በየክልሉ የስራ ቋንቋ ስለመተርጎሙ በተመለከተ ........ 16
የመንግስትን የግዥ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 17
የዕቃ፣ ግንባታና አገልግሎት ግዥ/የጨረታ ሂደቱን በተመለከተ ........ 17
የሚዲያ ማዕከል ግንባታ አማካሪ ድርጅትን በተመለከተ ........ 19
ለፕሮጀክቱ ስራ የተገዙ ዕቃዎች በስፔስፊኬሽኑ መሠረት ስለመግባታቸው የሚጋገጥ መሆኑን በተመለከተ 20
የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ማበልጸግና ፓይለት ማድረግን ሶፍትዌር ማልማት በተመለከተ ........ 21
የኢንፍራስትራክቸር እቃ ግዥ በተመለከተ ........ 22
የሚዲያ ማዕከሉን ግንባታ የውል ስምምነት በተመለከተ ........ 23
የበለፀገውን ሶፍትዌር በተመረጡት ማዕከሎች ማዘርጋትን (ሲስተሙን ማስፋፋትን) በተመለከተ ........ 25
ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደርጉ ክልሎች ለፕሮጀክቱ ዓላማ ግብአቶች መዋሉን በተመለከተ ........ 26
ለሲስተሙ ተጠቃሚዎች በቂ ስልጠና መስጠትን በተመለከተ፤ ........ 28
የክልሎች የሚገነቡ የስልጠና ማዕከል ግንባታ በተመለከተ ........ 28
ስልጠና በእቅድ መሰረት መፈፀሙ በተመለከተ ........ 30
ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ ........ 31
እቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተመለከተ ........ 33
ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአመታዊ ሪፖርት ግብረ መልስ ስለመስጠቱ በተመለከተ ........ 33
ቋሚ የግንኙነት መድረክ ስለመኖሩ በተመለከተ ........ 34
ክፍል ሶስት ........ 36
መደምደሚያ ........ 36
ክፍል አራት ........ 39
የማሻሻያ ሀሳብ ........ 39
አባሪ 1፡ ........ 42
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት( Evaluative Criteria) ........ 42
አባሪ 2 ........ 45
በናሙና የተመረጡ የፌዴራልና የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በአካል በሜድ ሚዲያ የተሰበሰበባቸው ........ 45
አባሪ 3 ........ 48
የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የስራ ሂደት መግለጫ ........ 48

## ማጠቃለያ / Executive summary/

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን እና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች መሰረት የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ከ2004 እስከ 2009 በጀት አመት በተከናወኑ ተግባሮች የክዋኔ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን የኦዲቱን ኃላማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ሲሆን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ስር የሚገኘውን ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተቋቋመበትን አላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ድጋፍ ለማድረግና የሀገሪቱን የመንግሥት ተቋማት የሰው ሃብት መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዳታ ቤዝ ማደራጀት እንዲሁም በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ያሉትን ችግሮች በመለየት ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሲሆን፣ ከ2004 እስከ 2009 ባሉት አምስት አመታት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 77 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ በናሙና ከተመረጡት 11 ተቋማት ማለትም (ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ቴክኒክና ስልጠና ኤጀንሲ፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጲያ ስራ አመራር ኢንስቲዩት፣ ከፌዴራል ትራንስፓርት ባለስልጣን፣ ከኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከከተማ ልማት ሚኒስቴር) እንዲሁም ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 89 የክልል ተቋማት ውስጥ በናሙና ከተወሰዱ ከ23 ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ማለትም ከ4 የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮዎች (ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር)፣ ከ2 የከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት (ከደብረማርቆስ እና ፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር)፣ ከ6 የዞን ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤቶች (ደብረማርቆስ፣ ፍኖተሰላም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሀዲያ፣ ወላይታሶዶ እና ሲዳማ ዞኖች)፣ ከ3 ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤቶች (ከቦሌ ፣

ከየካ እና ከአራዳ ክፍለከተማ)፣ ከ9 ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤቶች (ከጎዛመን፣ ከባህርዳር ዙሪያ፣ ከማቸከል፣ ከጃቢጠና፣ ከግራር ጃርሶ፣ መስቃያ፣ ከሌሞ፣ ከወላይታሶዶ ዙሪያ፣ ከሺበዲኖ ወረዳዎች) የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በመከለስና የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን የኦዲት ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

ኦዲቱ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በተቋቋመው የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ባደረጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ኦዲቱ ለሶስተኛ ወገን በቀላል አቀራረብ ግልፅነት እንዲኖረው ታስቦ በአጠቃላይ ከ19 መመዘኛ መስፈርት ውስጥ ዋና ዋና ግኝቶች ለማሳያነት በጉልህነት የተመረጡት ግኝቶች እና ማሻሻያ ሀሳቦች እንደመመዘኛ መስፈርቱ ቅደም ተከተል መሰረት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## ፕሮጀክቱ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት እና አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮለት ወደ ስራ መግባቱን በተመለከተ

- ✓ ፕሮጀክቱ በ2004 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ አመት ጀምሮ በሦስት ተከታታይ አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም የፕሮጀክቱ አደረጃጀትና በጀት ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ፀድቆ የመጣው በግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም. እንደሆነና እስከ ሚያዝያ 2006 ዓ.ም. ድረስም የራሱ የሆነ ፕሮጀክት ፅ/ቤትና ፕሮጀክትሥራ አስኪያጅ አለመመደቡን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ፕሮጀክቱ የሚመራበት የአፈፃፀም መመሪያ መኖሩን በተመለከተ

- ✓ በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 11 የፌዴራል እና 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቅም የአፈፃፀም መመሪያ እንዲደርሳቸው ያልተደረገ መሆኑን ለተቋማቱ የሚመለከታቸው ኋላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅና በተደረገ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የዕቃ፣ ግንባታና አገልግሎት ግዥ/ የጨረታ ሂደቱን በተመለከተ

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመረጃ ማዕከሉ እቃ ግዥ በብር 12,480,054.38፣ ለመረጃ ማዕከሉ ግንባታ ስራ ብር 1,512,940.00 እና የማማከር ስራ ብር 756,470.00 ብር በድምሩ ብር 14,749,464.38 ስራን ያለምንም ጨረታ ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የሰጠና ውል የተዋዋሉ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌላ ዘዴ ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የዳታ ማዕከሉን ግንባታ በተመለከተ

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀን 16/10/2007 ዓ.ም. ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ ግብአት ግዥ ቅድመ ክፍያ ብር **12,480,054.38** ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የከፈለ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከሁለት አመት ከአምስት ወር በኋላ በብር 7,150,964.85 የተገዛ ለዳታ ማዕከል ግንባታ የሚውል ዕቃ በቀን 24/04/2010 ዓ.ም. ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረት ክፍል ያስገባና ሂሳቡም እንዲወራረድ ያደረገ ቢሆንም ቀሪውን የብር 5,323,089.53 ዕቃ ማቅረብ ባለመቻሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤጀንሲው ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ በቀን 26/04/2010 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር ፐ/ሡ/ል/ሚ/ ፍግ/199/2010 በተፃፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን፣

## የበለፀገውን ሶፍትዌር በተመረጡት ማዕከሎች መዘርጋትን (ሲስተሙን ማስፋፋትን) በተመለከተ

- በኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተወሰዱት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ ዝርዝራቸው በአባሪ ከተያያዘ 11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስተቀር የወረዳ ኔት ቢኖራቸውም የሠራተኞችን መረጃ ወደ ተዘጋጀው ሲስተም የማስገባት ስራ ያልተጀመሩ በመስክ ምልከታ ታውቋል፣

### ድጋፍና ክትትል በተመለከተ

- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፓይለት ሳይቶችን (በ2007 በጀት ዓመት ኘሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት ) ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል አነስተኛ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት አመት ለተካተቱ ሁሉም ተቋማት በአካል እየተገኙ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ትግበራ እንዲገቡ የማድረግ ስራ ያልተሰራ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- በኦዲት ቡድኑ በናሙና በታዩት ከ11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ከገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስተቀር በቀሪዎቹ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስራ ወቅት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ጥያቄ ቢያቀርቡም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መፍትሄ ያልተሰጠ መሆኑ በቃለመጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመለየት፣ የተቋማቱን እቅድ አፈጻጸም በመከታተል ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

### ቋሚ የግንኙነት መድረክ ስለመኖሩ በተመለከተ

✓ በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 11 የፌዴራል እና 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበት ሁኔታ ለማወቅ ለወደፊትም በምን መንገድ ስራዎችን ማከናወን እንዳለባቸው ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ የሌለ መሆኑን እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የግንኙነት ጊዜ ስለመኖሩ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፡፡

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት ከተዘረጋ ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ሆኖታል፡፡ በእነዚህ ዘመናት መላውን የመንግስት ተቋማት ባለው አቅም ሲያገለግል ኖሯል፡፡ በተለያየ የአወቃቀር ሁኔታ ውስጥ ያለፈው ይህ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ የቀድሞውን የአቅም ግንባታ ሚኒስቴርን እና የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን በአንድ ላይ በማዋሐድ የሲቪል ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በመባል በአዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ/ም ተቋቁሟል፡፡
2. ይህ ተቋም በማቋቋሚያ አዋጁ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት መ/ቤቶች፣ የመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤ የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ በቀጣይነት የሚሻሻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ የፐብሊክ ሰርቪሱ ሰው ሃብት አመራር መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ያደርጋል፤ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡
3. በአሁኑ ወቅት በሰው ሀብት መረጃ ዙሪያ የሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ክፍተኛ ጊዜና የሰው ኃይል መውሰዱ እና ተገልጋዮችንም ማጉላላት እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ ችግሮች በመኖራቸው፤ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ልማታዊና ቀልጣፋ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን መገንባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አፅንኦት ተሰጥቶት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክት እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡
4. የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም/INTEGRATED CIVIL SERVICE MANAGEMENT SYSTEM/ ፕሮጀክት እጅግ ሰፊና ለሀገራችን የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ልማት ወሳኝ ሚና የሚጫወት ሲሆን፣ ከዚህ በፊት የነበረውን የመረጃ አያያዝ ችግር ይፈታል ተብሎ ይታመናል፡፡
5. ፕሮጀክቱ ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረውን የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ዘዴን አውቶሜት በማድረግ ማዘመንን፣ የመረጃ ሃብቱን አደረጃጀትና አጠቃቀምን ቀላልና

ምቹ በማድረግ ተደራሽነቱን ከፍ ማድረግን፣ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ቀላልና ቀልጣፋ ማድረግን ዋና ዋና አላማዎቹ በማድረግ የሚፈፀም ነው፡፡

6. የፕሮጀክቱ ባለቤት የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሲሆን፣ ፕሮጀክቱን ለማንቀሳቀስ የራሱ የሆነ የፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ፕሮጀክት ኃላፊ፣ ምክትል ፕሮጀክት ኃላፊ  እንዲሁም ከፕሮጀክት ማናጀሩ ጋር አብረው የሚሠሩ አማካሪዎችና ባለሙያዎችም እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

## የፕሮጀክቱ ደሰሳ

## የፕሮጀክቱ አስፈላጊነት/Rationale/

7. የሲቪል ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በአንድ መልኩ የሰው ሃብት ልማት ሪፎርም አጠናክሮ እየተገበረና እያስተገበረ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል የሰው ሃብት አመራሩን የበለጠ ጠንካራ ለማድረግ ደንቦችንና መመሪያዎችን እያዘጋጀ እንዲሁም አፈፃፀማቸውን እየተከታተለ እና  እየገመገመ ለመልካም አስተዳደር መስፈንና ለፈጣን አገልግሎቶች መረጋገጥ የበኩሉን ሁሉ ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡

8. ሆኖም ይህን ሁሉ እየሠራ እያለ መሥሪያ ቤቱ ከክፍተቶች የፀዳ አልነበረም፡፡ ከእነዚህ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ፡-

   - የሰው ሃብት መረጃ በወረቀት ብቻ የተያዘ መሆኑና ከብዙ ጊዜ አገልግሎት የተነሳ በመበላሸቱ የሠራተኛው መረጃ እየጠፋ መሆኑ፤
   - በፌዴራል በክልልና በከተሞች መካከል የሚደረገው የሰው ሃብት የመረጃ ልውውጥ ሁኔታ ጉታችና አስቸጋሪ መሆኑ፤
   - ተቋማዊና ግለሰባዊ መረጃዎች በሚገባው ተደራጅተው አለመጠበቃቸው፣
   - በወረቀት የሚገኙ መረጃዎች በብዙ ኮፒ አድርጎ ማስቀመጥ አስቸጋሪና አዋጪ አለመሆኑ፤
   - በሰው ሀብት መረጃ ዙርያ የሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ክፍተኛ ጊዜና የሰው ሀይል መውሰዱ እና ተገልጋዮችንም ማጉላላቱ፤
   - ፋይሎችን ደርድሮ መያዝ ብዙ ቦታ የሚይዝና መረጃ ፈልጎ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የሚፈጅ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

9. ስለዚህ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ልማታዊና ቀልጣፋ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን መገንባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክት ተዘጋጅቷል፡፡

## የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች

10. የተቀናጀ ሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ሁሉም የፌዴራልና የክልል መንግስታት መሥሪያ ቤቶች ናቸው፡፡ በተለይም የሲቪል ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሰው ሃብት መረጃ ዳይሬክቶሬት፣ በየፌደራል መስሪያ ቤቱ የሚገኙ የሰው ሃብት አመራር የሥራ ክፍሎች፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎችና የሰው ሃብት የሥራ ክፍሎች፣ በዞን፣ በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ የሚገኙት መሥሪያ ቤቶች የዚሁ ፕሮጀክት ውጤት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

11. እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አካላት በቀጥታ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፣ በተዘዋዋሪ ህዝቡና የሃገሪቱ ማህበረሰብ የፕሮጀክቱ ውጤት ከሆነው የሰው ሃብት መደራጀት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በሌላ አባባል ከፕሮጀክቱ ውጤት ሃገሪቷ የልማት ዕቅዶችን ዕውን ለማድረግ ያላትን የሰው ሃብት በአግባቡ አደራጅታና አስተባብራ ለበለጠ ልማት እንድትተጋ ያደርጋል፡፡

## የፕሮጀክቱ ዓላማ

12. የፕሮጀክቱ ዋና አላማ የሀገሪቱን የመንግሥት ተቋማት የሰው ሃብት መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዳታ ቤዝ ማደራጀት ነው፡፡ በመንግስታዊ ተቋማት የሚገኘውን ሲቪል ሰርቫንት የቅጥር፣ የዕድገት፣ የዝውውር እና የስንብት ሁኔታ ለመመዝገብና የተገኘውን መረጃ ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ፣ ታራሚ፣ ተስተካካይና ለክትትልና ግምገማ አመቺ እንዲሆን ማድረግ ቁልፉ ነገር ነው፡፡ ዝርዝር አላማዎቹም፡-
    - ነባሩን የሰው ሃብት የፋይል አያያዝ ዘዴ አውቶሜት ማድረግ፣
    - የሰው ሃብት መረጃን በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ፣
    - የሰው ሃብት መረጃ አደረጃጀትና አጠቃቀምን ቀላልና ምቹ ማድረግ፣

- የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ቀላልና ቀልጣፋ ማድረግ እና
- በጥናት ላይ ተመስርቶ የመረጃ ቋት ማዕከል (Data Center) መገንባት ናቸው፡፡

## የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ተግባራት

13. እነዚህን ከላይ የተገለፁትን አላማዎች እውን ለማድረግ በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የፕሮጀክቱን ጥቅል ሥራ ቢጋር (High level TOR ) ማዘጋጀት፣
2. በጥቅል ቢጋሩ ላይ በበመሥረት ለአማካሪ ድርጅቶች የፍላጐት መግለጫ (Request for Expression of Interest) ጨረታ ማውጣት፣
3. የጨረታ ሰነድ (RFP) ማዘጋጀት ፤
4. በፍላጐት መግለጫው ምዘና ውጤት መሠረት ለተመረጡ ድርጅቶች የጨረታ ሰነድ (RFP) ማሠራጨት፤
5. በጨረታው (በRFP) መሠረት ለውድድር የቀረቡ ሰነዶች (ፕሮፖዛሎች) ግምገማ ማድረግ፣ አሸናፊውን መለየት እና ማሳወቅ፤
6. ከአሸናፊው ኩባንያ ጋር ውለታ መፈራረም፤
7. የሲስተሙን ዝርዝር ፍላጐት ጥንቅር እና የኢንፍራስትራክቸር ፍልጎትን በማጥናት ንድፍ ማዘጋጀት፣
8. በተዘጋጀው ዲዛይን መሠረት የተቀናጀ ሲቪል ሰርቪስ ማኔጅሜንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ሶፍትዌር ማበልጸግ (ደቨሎፕ ማድረግ)፣ መፈተሽና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ፤
9. በተዘጋጀው የኢንፍራስትራክቸር ንድፍ መሠረት ሀርድዌርና ሶፍትዌር መግዣ የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፤
10. በጨረታው (በRFP) መሠረት ለውድድር የቀረቡ ሰነዶች (ፕሮፖዛሎች) ግምገማ ማድረግ፣ አሸናፊውን መለየት እና ማሳወቅ፤
11. ከአሸናፊው ሀርድዌርና ሶፍትዌር አቅራቢ ኩባንያ ጋር ውለታ መፈራረም፤
12. በተዘጋጀው የኢንፍራስትራክቸር ንድፍ መሠረት የመረጃ ቋት ማዕከል መገንባት፤
13. ለሲሰተሙ ተጠቃሚዎች በቂ ሥልጠና መስጠት፤
14. ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክ ድጋፍና የጥገና አገልግሎት መስጠት፤
15. በቀጣይ የተዘጋጀውን ሲስተም የማስፋፊያ ስራ በምዕራፍ ከፋፍሎ ለፌዴራል እና ለክልል ሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶች መትከል /መዘርጋት ናቸው፡፡

## የፕሮጀክቱ ወሰን

14. የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅሜንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም (የተ.ሲ.ማ.ኢ.ሲ) ፕሮጀክት በምዕራፍ ተከፋፍሎ የሚከናወን ሲሆን፣ በመጀመሪው ምዕራፍ የተቀናጀው ሲስተም በሲቪል ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት፣ በ2 የፌደራል እና በ2 የክልል መ/ቤቶች ይዘረጋል ወይም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ትግበራ ከሚገኘው ልምድ በመነሳት የቀሪዎቹ የ152 የፌደራልና የ273 የክልል መንግሥት መ/ቤቶች የማገናኘት ወይም ሲሰተሙን የመዘርጋት ሥራ ዕቅድ ተነድፎ በ 5 ኣመት ጊዜ ውስጥ በሚወሰነው ቅደም ተከተል መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## የፕሮጀክቱ ውጤት

15. የተቀናጀ ሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክት ዋና ዋና ውጤቶች ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት ናቸው፡፡

   1. በፌዴራል ደረጃ ማዕከላዊ የሆነ የሰው ሀብት መረጃ ማዕከል (Electronic Database) ይገነባል፡፡
   2. የፌደራልና የክልል መንግስታት ተቋማት ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሠራተኞች መረጃ ኤሌክትሮኒካል ይመዘገባል፣ ይያዛል ለሥራ ሲፈለግ በቀላሉ ተደራሽ ይሆናል፡፡
   3. እያንዳንዱ የመንግስት ሠራተኛ የራሱን ከሥራ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በቀላሉ ሊያገኝ ይችላል፡፡
   4. ችግር እያለባቸው ከመሥሪያ ቤት መሥሪያ ቤት እየቀያየሩ የሚኖሩትን ሠራተኞች ለማወቅና ለመከታተል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
   5. መረጃው በዳታ ቤዝ በመቀመጡ አሁን በወረቀት ፋይል ላይ የሚሠሩት ሠራተኞች  የመተንፈሻ አካላት ከኢንፌክሽን ስጋት ነፃ ይሆናሉ፡፡
   6. የሠራተኛ መረጃ ዘመናዊና ደህንነቱ በተረጋገጠ ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ ስለሚቻል የመረጃ መጥፋት ችግርን ሊታይ በሚችል ደረጃ ለመቀነስ ይቻላል፡፡
   7. የሃገሪቷን የሰው ሃብት አቅምና ፍላጐት በቀላሉ ለማጥናትና ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

## ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ኃይል

16. የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ፕሮጀክት ተጠሪነቱ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በአስተባባሪ ኮሚቴ በኩል ክትትልና ድጋፍ የሚደረግለት ነው፡፡
17. ፕሮጀክቱ አንድ ዋና ፕሮጀክት ማናጀር ያለው ሲሆን፣ በዋና ማናጀሩ ስር ምክትል ፕሮጀክት ማናጀር፣ የሲስተም ዳታ ቤዝና ኔትወርክ አስተዳደር፤ የዳታ አሰባሰብና ምዝገባ፣ የስልጠናና የሰው ሀብት መረጃ ቡድን መሪዎች አሉት፡፡
18. በሲስተም ዳታቤዝና ኔትወርክ አስተዳደር ቡድን መሪ ስር የሲሰተም ዳታቤዝ ባለሞያዎች እና የኔትወርክ አስተዳዳር ባለሞያዎች የሚገኙ ሲሆን፣ የዳታ ሰብሳቢ እና የዳታ አስገቢ ባለሞያዎች ደግሞ በዳታ አሰባሰብና ምዝገባ ቡድን መሪ ስር እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የስልጠና ባለሙያዎች፣ የሰው ሀብት መረጃ ባለሙያ፣ የሰው ሀብት ሥራ አመራር ባለሙያ፣ የአደረጃጀትና የሥራ ምዘና ባለሙያ፣ የአስተዳደር ፍ/ቤት ዳኛ፣ የኢንስፔክሽን ባለሙያ እና የህዝብ ግንኙነት፣ የድጋፍና ክትትል ባለሙያዎች በስልጠና የሰው ሀብት መረጃ ቡድን መሪ ስር ሆነው ይመራሉ፡፡
19. ለፕሮጀክቱ ስራ 64 ባለሙያዎች እንደሚያስፈልጉት በመዋቅር የተፈቀደ ቢሆንም እስከ ህዳር 30/03/2010 በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 56 ባለሙያዎች (87.5%) ነው፡፡

## የፕሮጀክቱ የፋይናንስ ምንጭ

20. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሥራው ማስኬጃ የሚጠቀመው ገንዘብ ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት ነው፡፡ ፕሮጀክቱን ተፈፃሚ ለማድረግም በ2004 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ አመት ጀምሮ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን፣ የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት ከ2005-2006 ዓ.ም ድረስ ሶፍትዌር የማልማት ስራ የተሰራ ሲሆን፣ ከ2007-2011 ዓ.ም ባሉት ተከታታይ አምስት አመታት ደግሞ የትግበራ ስራ የሚሰራበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሁሉም ምዕራፍ አጠቃላይ የወጪ ግምት ብር 272,021,294.00 እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አጠቃቀሙ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | በጀት ዓመት | ለፕሮጀክት የፀደቀ በጀት/በብር/ | ለፕሮጀክት የወጣ ወጪ/በብር/ | በጀት አጠቃቀም /በመቶኛ/ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2004 ዓ.ም | -------------- | --------------- | --------------- |
| 2. | 2005 ዓ.ም | -------------- | --------------- | --------------- |
| 2 | 2006 ዓ.ም | 15,000000.00 | 445,682.87 | 34% |
| 3 | 2007 ዓ.ም | 50,475,500.00 | 3,345,455.28 | 6.6% |
| 4 | 2008 ዓ.ም. | 55,799,900.00 | 45,554,671.06 | 81.6% |
| 5 | 2009 ዓ.ም | 56,620,000.00 | 26,712,086.64 | 47.17% |

ሠንጠረዥ 1፡- ከ2005 እስከ 2009 ዓ.ም. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በጀት አጠቃቀም

## የፕሮጀክቱ ስጋቶች(Project Risks)

21. የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም መረጃን በኤሌክትሮኒክስ ዳታቤዝ ለማደራጀት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል እንዲሁም የሠራተኞችን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከፍ ያደርጋል፡፡ ይህም ሀገሪቱ ለተያያዘችው የለውጥና የልማት ሥራ ጉልህ የሆነ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በአንጻሩ የሚዘረጋው ሥርዓት በይዘቱ የተወሳሰበ በመሆኑ የተለያዩ ስጋቶች ይኖረዋል፡፡ በዋናነት ቀጥሎ የተጠቀሱት በፕሮጀክት አፈጻጸሙ ላይ ስጋት የሚያሳድሩ ይሆናሉ፡-

    1. አጠቃላይ የሲቪል ሰርቪስ አግልግሎት አሰጣጥ በኮምፒውተር ስለሚቀየር በቀጥታ ሥራው ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ክህሎታቸውን ማሳደግ ይጠይቃል፤ ስለሆነም በስራው ላይ ለሚመደቡ ሰራተኞች ቅድመ ትግበራ ስልጠና ሲለሚያስፈልጋቸው አስቀድሞ ሊታሰብበት ይገባል፡፡
    2. የሲቪል ሰርቪሱ መረጃ ልውውጥ የሚደረግበት መረብ ለግለሰቦች መረጃ የመሠረቅ አደጋ ሊጋለጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም የሚዘጋጀው የኢንፍራስትራክቸር ሥርዓት ተፈለጊውን የመረጃ ደህንነት የሚያስጠብቅ መሆን ይገባዋል፡፡ ይህም የፕሮጀክቱን ዋጋ በአንጻራዊነት ከፍ ያደርገዋል፡፡

3. የፕሮጀክቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ አስተዋጽዖ ከሚያደርጉት አንዱ ብቃት ያለው የቴክኒክ ሙያተኛ ነው፡፡ ከልምድ እንደሚታየው በትግበራ ሂደት የተሳተፉትን ወይም ብቃት ያላቸውን ሞያተኞች ማቆየት በተለያዩ ምክንያቶች አስቸጋሪ ነው፤ ይህም ፕሮጀክቱን ከፍተኛ ስጋት ላይ ይጥለዋል፡፡ ስለዚህ ከወዲሁ በዚህ ዙሪያ ተገቢው ዝግጅት ሊደረግ ይገባል፡፡
4. ፕሮጀክቶች በባሕሪያቸው ለውጥ ያካትታሉ፣ በማወቅ ወይም ባለማወቅ ብዙ ሰራተኞች ለውጡን ይቃወማሉ ሲከፋም ያደናቅፋሉ፤ ከልምድ እንደሚታየው ይህ ከፍተኛ የፕሮጀክት ስጋት በመሆኑ ከፍተኛ የማስተዋቅ ስራ በመስራት በተቃዋሚነት ሊሰለፍ የሚችለውን አብዛኛውን ሰራተኛ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡
5. የፕሮጀክቱ ወሰን ሰፊ በመሆኑ በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ ከወዲሁ የፋይናንስ ምንጮችን ማፈላለግ ያስፈልጋል፡፡
6. የተቀናጀ ሥርዓቱ የሚዘረጋባቸው መ/ቤቶች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በቂ ዝግጅት ላያደርጉ ይችላሉ፤ ይህም ፕሮጀክቱ እንዲጓተት ምክንያት ስለሚሆን፣ የሚመረጡት የፌደራልና የክልል መ/ቤቶች ከፍተኛ ኃላፊዎች በፕሮጅክት አመራሩ ላይ የሚወከሉበት አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡
7. ማዕከላዊ የሆነ አሰራር ለመዘርጋት የኢትዮ ቴሌኮም መሠረተ ልማት አቅርቦት ሳይቆራረጥ መቅረብ ይኖርበታል፣ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የመንግሥት ተቋማት የራሳቸው ሰርቨሮች ሊኖሯቸው ያስገድዳል፡፡
8. ስምን መሠረት ያደረገ ሲቪል ሰርቫንት መረጃ አደረጃጀት በመረጃ ቋት ውስጥ (uniquely) ተለይቶ መታወቅ አዳጋች ነው፤ በመሆኑም ዜጎች ወይም ግብር ከፋዮች በብቸኝነት ተለይተው ከሚታወቁበት አሰራር ጋር የተቀናጀ ስርዓቱን ማስተሳሰር ያስፈልጋል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

22. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር እተተገበረ የሚገኘው የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር የሀገሪቱን የመንግሥት ተቋማት የሰው ሃብት መረጃ በኤሌክትሮኒክስ

ዳታ ቤዝ በማደራጀት በመንግስታዊ ተቋማት የሚገኘውን የሲቪል ሰርቫንት የቅጥር፣ የዕድገት፣ የዝውውር እና የስንብት ሁኔታ ለመመዝገብና የተገኘውንም መረጃ ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ፣ ታራሚ፣ ተስተካካይና ለክትትልና ግምገማ አመቺ እንዲሆን የማድረጉን ተግባር ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ

23. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር እተተገበረ የሚገኘውን **"የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት አፈፃፀምን መገምገም"** የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) እና መመዘኛ መስፈርቶች

24. ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ስር ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issue/ ተመርጠዋል፡፡እነርሱም፡

   I. ፕሮጀክቱን በታቀደለት ጊዜ እና ወጪ ተግባራዊ ለማድረግ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል የሚከናወኑ የንብረት እና የአገልግሎት ግዥዎች በመንግስት ግዥ መመሪያ መሰረት መፈፀሙን፣ የተገዙት ንብረቶችም ለፕሮጀክቱ ዓላማ መዋሉን እንዲሁም ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ የተደረጉ መሆኑን መገምገም፣

   II. ስለሚዘረጋው ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት አጠቃቀም በተመለከተ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደረጉ የፌዴራልና የክልል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚደረገው የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የትምህርትና ስልጠና እንዲሁም በትግበራ ወቅት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

   III. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆነው ስራ ተፈፃሚ ለማድረግ እንዲያስችለው ከባለድርሻ አካላት ( ኢትዮ ቴሌኮም፣ የመገናኛ እና

ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር እና የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ) እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለሚያከናውናቸው ስራዎች የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት የተጠናከረና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉት ናቸው፡፡

25. እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 18 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (evaluative criteria) የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፓርት ጋር በአባሪ ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

26. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian performance Audit standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም. በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ የዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጀምሮ ማለትም 2005 እስከ 2009 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ስራ ነው፡፡

27. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሲሆን፣ ከ2004 እስከ 2009 ባሉት አምስት አመታት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 77 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ በናሙና ከተመረጡት 11 ተቋማት ማለትም (ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ቴክኒክና ስልጠና ኤጀንሲ፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከኢንዲስትሪ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጲያ ስራ አመራር ኢንስቲዩት፣ ከፌዴራል ትራንስፓርት ባለስልጣን፣ ከኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከከተማ ልማት ሚኒስቴር) እንዲሁም ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 89 የክልል ተቋማት ውስጥ በናሙና ከተወሰዱ ከ23 ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ማለትም ከ4 የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮዎች (ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር)፣ ከ2 የከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት (ከደብረማርቆስ እና ፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር)፣ ከ6 የዞን ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤቶች (ደብረማርቆስ፣

ፍኖተሰላም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሀዲያ፣ ወላይታሶዶ እና ሲዳማ ዞኖች)፣ ከ3 ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤቶች (ከቦሌ ፣ ከየካ እና ከአራዳ ክፍለከተማ)፣ ከ9 ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤቶች (ከጎዛመን፣ ከባህርዳር ዙሪያ፣ ከማቻከል፣ ከጀቢጠና፣ ከግራር ጃርሶ፣ መስቃያ፣ ከሌሞ፣ ከወላይታሶዶ ዙሪያ፣ ከሺበዲኖ ወረዳዎች) የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በመከለስና የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን የኦዲት ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

## የስራ ሂደት መግለጫ (process description)

28. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተዘጋጀው የተቋማት መምረጫ መስፈርት መሰረት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረግባቸውን ተቋማትን መርጠው እንዲልኩ ለክልል መንግስታት በደብዳቤ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያሳውቃል ፤ የፌዴራል ተቋማትን በመምረጫ መስፈርት መሰርት ፕሮፖዛል ለከፍተኛ አመራሩ ቀርቦ በማጸደቅ ወደ ስርዓቱ እንዲካተቱ ይደረጋል፤ ከወረዳ ኔት ጋር ያልተገናኙ ተቋማትን ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶች (መገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር እና ኢትዮ ቴሌኮም) ጋር በመተባበር በወረዳ ኔት ጋር እንዲተሳሰሩ ይደረጋል ፤ የወረዳ ኔት ጋር የተገናኙ ተቋማትን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ወደ ሲሰተሙ እንዲገቡ የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፤ በተመረጡ ተቋማት ላይ ለፕሮጀክት ስራው አሰፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመሰብሰብ ፤ የተሰበሰበው መረጃ ወደ ተዘረጋው የመረጃ አያያዝ ስርዓት ውስጥ እንዴት እንደሚገባ እና የሲስተም አጠቃቀም ስልጠናዎች በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ይሰጣል፤ ተቋማቱ ከዋናው የመረጃ ማዕከል ጋር እንዲገናኙ የሚያስችል የራሳቸው የሆነ አይፒ (IP ) አድራሻ ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር በማስፈቀድ እና በኢትዮ ቴሌኮም አማካኝነት ወደ ወረዳ ኔት (VPN) እንዲገናኙ ይደረጋል፤ በተሰጣቸው አድራሻ መሰረት ተቋማቱ የሰበሰቡትን የሰራተኞች መረጃ ወደ ሲሰተሙ ያስገባሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### አደረጃጀትንና መመሪያዎችን በተመለከት

#### ፕሮጀክቱ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት እና አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮለት ወደ ስራ መግባቱን በተመለከተ

29. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተቀመጠለት መዋቅር /አደረጃጀት ጥናት/ መሰረት የተዋቀረ መሆኑንና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከውስጥና ከውጪ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
30. ፕሮጀክቱ በ2004 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ አመት ጀምሮ በሦስት ተከታታይ አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም የፕሮጀክቱ አደረጃጀትና በጀት ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ፀድቆ የመጣው በግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም. እንደሆነና እስከ ሚያዚያ 2006 ዓ.ም. ድረስም የራሱ የሆነ ፕሮጀክት ፅ/ቤትና ፕሮጀክትሥራ አስኪያጅ አለመመደቡን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
31. ፕሮጀክቱ የራሱ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ እንደሚኖረው፣ ከስራ አስኪያጅ ጋር በቅርበት የሚሠሩ አማካሪዎችና ባለሙያዎች እንደሚኖሩ፣ በዚህ አይነት የሚደራጀው የፕሮጀክት ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር እንደሚሆን እንዲሁም ፕሮጀክቱ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣ ከመገናኛና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩንኬሽን ሚኒስቴርና የሚመለከታቸው አካላት ተወጣጥቶ በሚቋቋም የበላይ ኮሚቴ /Steering Commitree/ እንደሚመራ የፕሮጀክቱ አደረጃጀት ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
32. ይሁን እንጂ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አስተባባሪ ኮሚቴ እንደሚያስፈልገውና እንደሚቋቋም ቢታመንም እስከ 2009 በጀት ዓመት ሶስተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ ተግባራዊ ሳይሆን እንደቆየ የፕሮጀክቱ የ2009 በጀት ዓመት የ9 ወራት አፈፃፀም ሪፖርት በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
33. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር ፐስሚ/ሚድ-157/09 በቀን ጥር 23/2009 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ለክልሎችና ለሚመለከታቸው አካላት አስተባባሪ

ኮሚቴ መድበው እንዲያሳውቁ ቢገለጽም ክልሎችም ሆኑ የፌዴራል ተቋማት ኮሚቴውን መድበው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለማሳወቃቸው የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

34. ጉዳዩን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ አስተባባሪ ኮሚቴ ከዚህ በፊት ተዋቅሮ የነበረ መሆኑና አንድ ዙር ስብሰባ ስለማድረጋቸው ገልፀዋል፡፡

35. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ ከዚህ በፊት የተቋቋመውን አስተባባሪ ኮሚቴ ዝርዝር እና አንድ ዙር ስብሰባ ስለማድረጋቸው የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

36. በመሆኑም ፕሮጀክቱ በ2004 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ አመት ተጀምሮ በሦስት ተከታታይ አመታት ውሰጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ቢታሰብም የራሱ የሆነ ፕሮጀክት ፅ/ቤት እና ኃላፊ ባለመመደቡ ስራው እንዲዘገይ እንዲሁም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲሚቋቋም ባለመደረጉ የፕሮጀክቱን የስራ እንቅስቃሴ በየጊዜው እየገመገመ በሌሎች ባለድርሻ አካላት በኩል መፍትሄ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በአጭር ጊዜ በመፍታት ፕሮጀክቱ በታለመለት ጊዜና ወጪ እንዳይጠናቀቅ አድርጎል፡፡

## ፕሮጀክቱ የሚመራበት የአፈፃፀም መመሪያ መኖሩን በተመለከተ

37. የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክትን በፌዴራልና በክልል ሲቪል ስርቪስ ቢሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ጽ/ቤቱ የአፈፃፀም መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

38. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን ከመጀመሩ በፊት የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ኃላፊነት፣ ኘሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት በኘሮጀክቱ ዙሪያ ያላቸው ሚና እስከምን ድረስ እንደሆነ የሚገልጽ እና ፕሮጀክቱ የሚመራበት የአፈጻጸም መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ለሚያደርጉት ለፌዴራል እና ለክልል ተቋማት ማሰራጨት እንዳለበት የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 11 የፌዴራል እና 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ

የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቅም የአፈፃፀም መመሪያ እንዲደርሳቸው ያልተደረገ መሆኑን ለተቋማቱ የሚመለከታቸው ኋላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅና በተደረገ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፕሮጀክቱ የአፈፃፀም መመሪያ እንደሚያስፈልግ ቢታወቅም በሂደት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንደሚዘጋጅ ገልፀዋል፡፡

41. በመሆኑም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የአፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ ባለማሰራጨቱ ክልሎች ዝርዝር ተግባራት አዘጋጅተው በወቅቱ ወደ ሥራ እንዳይገቡ፣ በክልል ደረጃ ፕሮጀክቱን በባለቤትነት የሚመራ አካል እንዳይኖር እንዲሁም በክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት፣ በዞንና ወረዳ ወቅቱን የጠበቀ ድጋፍና ክትትል እንዳይደረግ እና በአጠቃላይ ኘሮጀክት ጽ/ቤቱንና ክልሎችን የሚያስተሳስር የአሰራር ስርዓት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

## የተገልጋይ ማንዋል በየክልሉ የስራ ቋንቋ ስለመተርጎሙ በተመለከተ

42. ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚደረግባቸው የክልል የስራ ቋንቋዎች የስልጠና ማንዋሎችን በመተርጎም ለተገልጋዮች ተደራሽ ሊያደረግ ይገባል፡፡

43. በኦዲቱ ወቅት የፕሮጀክቱ የ2007 ዓ.ም.፣ የ2008 ዓ.ም. እና 2009 ዓ.ም የበጀት አመት የዕቅድ ሪፖርቶች በተከለሰበት ወቅት የስልጠና ማንዋሎችን በኦሮሚኛና በትግርኛ ቋንቋዎች በመተርጎም ስራውን ለሚሰሩ አካላት ተደራሽ ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ይሁን እንጂ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የስልጠና ማንዋሎቹ በክልሎች የስራ ቋንቋ ማለትም/ በኦሮምኛና በትግርኛ ቋንቋ/ ተተርጉመው ለተገልጋይ ተደራሽ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

45. ስለ ጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከክልሎች ጋር በመሆን የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ እንደተተረጎመ ሁሉ ወደፊት ማንዋሎችም እንደሚተረጎሙ ገልፀዋል፡፡

46. የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት የስልጠና ማንዋል በክልሉ የስራ ቋንቋ ተተርጉሞ ለተገልጋይ ተደራሽ ባለመደረጉ የግንዛቤ ችግር እንዲፈጠር እና በክልሉ የሠራተኞች የመረጃ አያያዝ ስርዓት በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዳይሰራ ያደርጋል፡፡

## የመንግስትን የግዥ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

## የዕቃ፣ ግንባታና አገልግሎት ግዥ/ የጨረታ ሂደቱን በተመለከተ

47. ለተቀናጀ ሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም መረጃ ማዕከል ግንባታ የሚውል የእቃ ግዥ፣ የዳታ ማዕከሉን የግንባታ እንዲሁም የዳታ ማዕከል የማማከር ስራ ግዥ የመንግስት የግዥ ስርዓትን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

48. በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/1994 አንቀጽ 33 ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 3 ላይ በመንግስት ግዥ አፈፃፀም ስራ ላይ የሚውሉት የግዥ ዘዴዎችን በተመለከተ፣ በአዋጁ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም እንዳለባቸው እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ የተገለፁት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

49. በተጨማሪም በአዋጁ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 1ረ ላይ በተደነገገው መሰረት ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች (ማለትም በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ፣ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣ ውስን ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ እና ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ) የሚጠቀም ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከግልፅ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ዘዴዎች መከተል የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልፅ ሰነድ መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

50. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት የግዥ መመሪያን ተግባራዊ ስለማድረጉ በተደረገው የሰነድ ማጣራት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመረጃ ማዕከሉ እቃ ግዥ በብር 12,480,054.38፣ ለመረጃ ማዕከሉ ግንባታ ስራ ብር 1,512,940.00 እና የማማከር ስራ ብር 756,470.00 ብር በድምሩ ብር 14,749,464.38 ስራን ያለምንም ጨረታ ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የሰጠና ውል የተዋዋሉ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌላ ዘዴ ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመረጃ ማዕከሉን የግንባታ እቃ ያለትርፍ አቅርቦትና የማማከር አገልግሎትን ብቸኛ ለሆነው ለመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሲሰጥ በአዋጅ በተሰጠው መብት መሰረት መሆኑንና የሚገነባው ማዕከል በአገሪቱ ያለውን የሰው ሀብት መረጃ ደህንነት የሚጠብቅ የመንግስት ተቋም በመሆኑ ቀጥታ ያለጨረታ እንደተሰጠው ገልፀዋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የአምስት ሚሊዮን የሰራተኞች መረጃ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት ለማዘመን የመረጃ ደህንነት መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ እንጂ ሆን ተብሎ የመንግስት የግዥ መመሪያን ለመጣስ ተብሎ የተደረገ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ለግንባታው የሚያስፈልጉ ዕቃዎች አቅርቦትና በኔትወርክ ሲስተም ደህንነት ዙሪያ የማማከር አገልግሎት በውስን ጨረታ ለኢፌዴሪ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ መሰጠቱን፣ ኤጀንሲውም ለትርፍ ያልተቋቋመ የመንግሥት ተቋም በመሆኑ ምንም ዓይነት የዋጋ ልዩነት ሳይኖር ዕቃዎች በተገዙበት ዋጋ እንዲያቀርብ ውል የተፈፀመ መሆኑን እና መረጃው ከፍተኛ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው በቀላሉ እንዳይጠፋ ለማድረግ ሲባል ግንባታው በአገር በቀል የመንግሥት ተቋም እንዲከናወን ስለታመነበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

54. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ የመረጃ ማዕከሉን ግንባታ ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሲሰጥ ከተፈፀመ ውል ስምምነት እና የክፍያ ሰነድ ውጪ የመረጃ ማዕከሉ ግንባታ በውስን ጨረታ ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ስለመሰጠቱ የሚያሳይ ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 250/2004ን በከለሰበት ወቅት ኤጀንሲው በኢንፎርሜሽንና ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ደህንነት ዙሪያ መንግስትን ማማከር፣ ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረገ የቁልፍ ተቋማትን አቅም መገንባት፣ የኢንፎርሜሽንና ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማትን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችንና ስታንደርዶችን ማዘጋጀትና ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን መከታተል እንዲሁም ቁልፍ ተቋማት በብሔራዊ የኢንፎርሜሽን

ደህንነት ፖሊሲና ስታንደርድ ላይ የተመሰረተ የመረጃ ደህንነት ፖሊሲና ስታንደርድ እንዲኖራቸው መደገፍና በማንኛውም ጊዜ የቁጥጥርና የደሰሳ ጥናት ማካሄድ፣ የደህንነት ብቃት ደረጃ ሰርተፍኬት መስጠት ወይም በሌሎች አካላት እንዲሰጥ ውክልና መስጠት እንጂ የኢንፎርሜሽንና ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማትን ግንባታ እንደሚሰራ የሚገልፅ ነገር ባለመኖሩ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም ፡፡

55. በመሆኑም የመንግስት ግዥ ስርዓት ግልፅ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና አድልዎ የሌለበት እንዲሁም ለግዥ የሚውለው ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ በተሻለ አኳኋን ቁጠባን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ስለመደረጉ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## የመረጃ ማዕከል ግንባታ አማካሪ ድርጅትን በተመለከተ

56. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ አማካሪ ድርጅት ሊኖረው ይገባል፡፡
57. አንድ ድርጅት የግንባታ አገልግሎት በሚያከናውንበት ወቅት ስራውን ከሚሰራው አካል ውጪ ከግንባታው ጋር ግንኙነት የሌለው ገለልተኛ አማካሪ መኖር እንዳለበት መልካም ተሞክሮ እና የተለመደ አሰራር መሆኑ ይታወቃል፡፡
58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዳታ ማዕከሉን የማማከር ስራ ውል ግንባታውን ለሚያከናውነው ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በብር 756,470.00 የሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
59. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሠራተኛውን መረጃ በቀላሉ ከመጥፋት የሚታደግ ብቸኛ መንግስታዊ ድርጅት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በመሆኑ ሌላ ይህንን የሚሰራ የመንግስት አካል ባለመኖሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
60. የፕሮጀክቱ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ በሀገር ደረጃ የተለያዩ አገር በቀል አማካሪ ድርጅቶች እንዳሉ የሚታወቅ ከመሆኑ በተጨማሪ የማዕከሉ ግንባታም ሆነ የማማከር ስራ የሚሰራው በአንድ ተቋም በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም ፡፡

61. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዳታ ማዕከሉን ግንባታ የሚያከናውነው አማካሪ ድርጅት ገለልተኛ አካል ባለመሆኑ በሚገነባው ግንባታ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉድለቶች/ ከጥራት እና ከገንዘብ ጉድለት አንፃር/ ተለይተው እንዳይታወቁ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለፕሮጀክቱ ስራ የተገዙ ዕቃዎች በስፔስፊኬሽኑ መሠረት ስለመግባታቸው የሚረጋገጥ መሆኑን በተመለከተ

62. ለፕሮጀክቱ ስራ የጨረታ አሸናፊ ሀርድዌርና ሶፍትዌር አቅራቢ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው እቃዎች በውሉ ላይ በተቀመጠው በተወዳደሩበትና ባሸነፉበት ዝርዝር መግለጫ /specification/ መሰረት መሆኑን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት የጨረታ አሸናፊ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎች በዝርዝር መግለጫ (በስፔስፊኬሽኑ) መሠረት የተገዙ ስለመሆናቸው እየተረጋገጠ ወደ ንብረት ክፍል ስለመግባታቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚዋቀር የቴክኒክ ኮሚቴ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት የግዥ መመሪያ ሰነድ ላይ የተገለፀ ሲሆን፣ ይህ ስለመከናወኑ በተደረገው ማጣራት፤ለዳታ ማዕከሉ ኔትወርክ ዝርጋታ የሚያስፈልጉ የኔትወርክ ዕቃዎች ከአይ.ኢ. ኔትወርክ ሶሊውሽን በብር 23,606,440.44 ግዢ ተፈጽሞ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ ወደ ንብረት ክፍል የገቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. ይሁን እንጂ ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ የሚያስፈልጉት ዕቃዎች በኢንፎርሜሽንና መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በኩል ግዣቸው ተፈጽሞ አገር ውስጥ የገቡና ዕቃዎቹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረት ክፍል ስለመግባታቸው ሞዴል 19 የተቆረጠ ቢሆንም፣ ዕቃዎቹ በስፔሲፊኬሽኑ መሠረት መሆናቸውን አረጋግጦ የመረከቡ ሥራ ያልተከናወነ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በስፔስፍኬሽኑ መሰረት እየታየ ገቢ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

66. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ ለኦዲት ቡድኑ የተሰጠው መረጃ እቃዎች ወደ ንብረት ክፍል በሚገቡበት ወቅት መሟላት ያለባቸውን ዝርዝር ተግባራት ያላካተተ መረጃ የተሰጡ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

67.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዝርዝር መግለጫው መሰረት እቃዎችን ተረክቦ ያለመግባታቸው ለወጣው የመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኝ አገልግሎት ስለመገኘቱና እቃዎቹ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ስለማሟላታቸው ለማረጋገጥ እንዳይቻል አድረጎል፡፡

## የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ማበልጸግና ፓይለት ማድረግን ሶፍትዌር ማልማት በተመለከተ

68. የሶፍትዌር ማልማት ስራ በውል ስምምነት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፀሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

69. ኘሮጀክቱ በ2004 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ አመት ጀምሮ በሦስት ተከታታይ አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በእቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም የኘሮጀክቱ አደረጃጀትና በጀት ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ፀድቆ የመጣው በግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም. እንደሆነና እስከ ሚያዝያ 2006 ዓ.ም. ድረስም የራሱ የሆነ ፕሮጀክት ፅ/ቤት አልነበረውም፡፡ ይሁን እንጂ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንደነበሩ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. በዚህም መሰረት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከመቋቋሙ በፊት ፕሮጀክቱ ተቀርፆ የበጀት ማፈላለግ ስራ የተሰራ መሆኑን፣ የሲሰትም ሪኳይርመንት ተዘጋጅቶ ጨረታ የወጣና ፋይናንስና ቴክኒካል ግምገማ በማድረግ ያሸነፈው ድርጅት ተለይቶ ከአሸናፊው ኩባንያ ጋር ውለታ የተፈረመ መሆኑን፣ የሲስተም ጥናት ዝርዝር ፍላጎት በማጥናት ንድፍ ማዘጋጀት (Requirement gathering, system Design and Specification)፣ እና የኢንፍራስትራክቸር ዝርዝር ፍላጎት በማጥናት ንድፍ በማዘጋጀት ሲስተሙ እንዲለማ የተደረገ መሆኑንና የሲስተም ሪኳይርመንትና የሶፍትዌር ፍተሻ የተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. በተዘጋጀው ዲዛይን መሠረት የተቀናጀ ሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ሶፍትዌር ማበልጸግ (Software Development)፣ መፈተሽ (Testing)፣ ለአገልግሎት ብቁ ማድረግን በተመለከተ፡-

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሶፍትዌሩን ለማልማት በአለም አቀፍ የጨረታ ሂደት በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ እ.ኤ.አ. አኘሪል 22 ቀን 2012 (በ30/09/2004 ዓ.ም.) የወጣ እና ከከስተር ኮምፒውቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር

ውል የተፈራረመው እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 8 ቀን 2012 (28/01/2005 ዓ.ም.) መሆኑን፣ ይህም ከአምስት ወራት በላይ የፈጀ መሆኑን፣

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 8 ቀን 2012 (28/01/2005 ዓ.ም.) ከከስተር ኮምፒውቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር የሶፍትዌሩን ማልማት ሥራ በስድስት ወር ሰርቶ ለማስረከብ በብር **5,393,500.00** የተዋዋለ ቢሆንም፣ በተገባው ውል መሰረት ስራው ስለመስራቱ የተሟላ ማስረጃ ማለትም የመጨረሻው ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች እንዲያቀርብ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሰነዱን ማቅረብ ያልቻሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. የፕሮጀክቱ ኃላፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሶፍት ዌር ማልማት ሥራ በተገባው ውል መሠረት ስለመከናወኑ ገልጸዋል፡፡

73. የፕሮጀክቱ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2006 ዓ.ም. የታቀደው ተግባር በ2005 ዓ.ም. የተጀመረውን የሶፍትዌር ልማቱን በማጠናቀቅ ወደ ሙከራ ትግበራ ለማሸጋገር መሆኑንና በዚህም መሠረት የሶፍትዌር ልማቱ ተጠናቆና ለሙከራ የተመረጡ ተቋማት ባለሙያዎች በተፈለገው መልኩ መዘጋጀቱን በመፈተሽ የሰጡት ግብዓቶች በአልሚው ድርጅት ተካቶ ለሙከራ ዝግጁ እንደተደረገና በሶፍትዌሩ ልማት ላይ የተሳተፉ የፌዴራል መ/ቤቶች እና የሁለት ክልሎች (ከአማራና ከኦሮሚያ ክልሎች) ባለሙያዎች ሥልጠና እንዲወስዱ የተደረገ መሆኑን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2006 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ የተገለፀ መሆኑን፣ ይህም የሶፍትዌሩን ማልማቱ ሥራ ከአንድ አመት በላይ የፈጀ መሆኑን የሚያመላክት በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም ፡፡

74. የሶፍትዌሩ ማልማት ስራ በተገባው ውል መሠረት ባለመከናወኑ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት በጊዜ ሰሌዳው መሠረት እንዳይከናወን አድርጓል፡፡

## የኢንፍራስትራክቸር እቃ ግዥ በተመለከተ

75. የኢንፍራስትራክቸር እቃ ግዥ በውል ስምምነት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

76. በተዘጋጀው የኢንፍራስትራክቸር ንድፍ መሠረት የሀርድዌር ግዢ ማከናወን በተመለከተ፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በብር 23,393,500.00 (በዩ.ኤ.ስ ዶላር 1,186,724.40) የተለያዩ የኔትወርክ እቃዎችን አቅርቦት፣ የመገጣጠምና መስራታቸውን በማረጋገጥ የማስረከብ/Supply, Installation, Comissioningofnetwork infrastructure/ ስራ ውል ከአይ.ኢ. ኔትወርክ ሶሊሽን ጋር በሚያዚያ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. የተፈራረመ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- ✓ በውሉ መሰረትም ድርጅቱ ለዳታ ማዕከሉ የቀረቡት የኔትወርክ እቃዎች ተገጣጥመው ካለቁ በኃላ እቃዎቹ መስራትና ያለመስራታቸውን የማረጋገጥ ስራን ውሉ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ ባሉት 3 ዓመታት እንደሚያከናውን የተገለፀ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- ✓ የመረጃ ማዕከል ግንባታው ሳይጠናቀቅ የኔትወርክ እቃዎች ግዢ የተፈጸመ በመሆኑ ዕቃዎቹ አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የዋስትና ጊዜያቸውን የጨረሱ ስለመሆኑ በእቃ አቅራቢው ድርጅት ኢ.ኤ.አ. በኦገስት 21 ቀን 2017(በ/በ/2001 ዓ.ም.) በደብዳቤ ቁጥር IE/PMO/210817/01 በተፃፈ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

77. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኢንፍራስትራክቸር እቃ ወደ ስራ ያልገቡት የመረጃ/ዳታ ማዕከሉ ግንባታ እየተገባደደ ስለሆነ በጥቂት ጊዜ ተጠናቆ እቃዎቹ ወደ ስራ እንደሚገቡ ገልፀዋል፡፡
78. ስለጉዳዩ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የዳታ ማዕከሉ በወቅቱ ባለመገንባቱ የተገዙ እቃዎች በማዕከሉ መገጣጠም ሳይቻል በመቅረቱ እና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በአካል ተገናኝተው በጥቂት ቀናት ውስጥ የመገጣጠም ስራ እንደሚከናወን ገልፀዋል፡፡
79. በመሆኑም ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጥቶ የኢንፍራስትራክቸር እቃ ግዥ ወደ ስራ ባለመግባቱ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዳይሰራ አድረጎል፡፡

## የመረጃ ማዕከሉን ግንባታ የውል ስምምነት በተመለከተ

80. የፌዴራልና የክልሎች የዳታ ማዕከሉ ግንባታ በውል ስምምነት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

81. የዳታ ማዕከሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መከናወኑን በተመለከተ የሚከተሉት ነገሮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የመረጃ/ዳታ ማዕከሉን ግንባታ በ13 ወራት ሰርቶ ለማስረከብ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በቀን 19/09/2007 ዓ.ም. በብር 14,749,464.38 የተዋዋለ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ግንባታውን አጠናቆ ያላስረከበ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀን 16/10/2007 ዓ.ም. ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ ግብአት ግዥ ቅድመ ክፍያ ብር **12,480,054.38** ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የከፈለ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ዳታ ማዕከሉ ያልተቋቋመ በመሆኑ ለጊዜው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ባሉት ሁለት ሰርቨሮች የዳታቤዝ ሲስተሙን በመጫን ወደ ሥራ የተገባ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ጊዜያዊው የመረጃ ማዕከል መሟላት ያለባቸው ግብአቶች ማለትም የተሟላ የኤሌክትሪክ ሲስተም፣ ማቀዝቀዣ የመሳሰሉት ግብአቶች የተሟሉ ባለመሆናቸው መብራት በሚጠፋ ጊዜ ሲስተም የሚቋራረጥ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
- ✓ የመረጃ ማዕከሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በ4 የክልል ሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች ተገንብቶ ወደ ስራ መገባት እንዳለበት የፕሮጀክቱ ሮድ ማፕ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፣ በኦዲቱ በናሙና በታዩት ሶስት የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮዎች (አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ) ስለሚገነባው የመረጃ ማዕከል ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መረጃ የሌላቸው መሆኑን ከቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ማወቅ ተችሏል፤
- ✓ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከሁለት አመት ከአምስት ወር በኋላ በብር 7,150,964.85 የተገዛ ለዳታ ማዕከል ግንባታ የሚውል ዕቃ በቀን 24/04/2010 ዓ.ም. ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረት ክፍል ያስገባና ሂሳቡም እንዲወራረድ ያደረገ ቢሆንም ቀሪውን የብር 5,323,089.53 ዕቃ ማቅረብ ባለመቻሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤጀንሲው ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ በቀን 26/04/2010

ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር ፐ/ሠ/ል/ሚ/ ፍግ/199/2010 በተፃፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን፣

82. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመረጃ/ዳታ ማዕከሉ ግንባታ እየተገባደደ ስለሆነ በጥቂት ጊዜ ተጠናቆ እቃዎቹ ወደ ስራ እንደሚገቡ ገልፀዋል፡፡

83. በመሆኑም የዳታ ማዕከሉ ግንባታ በታቀደለት ጊዜ ተጠናቆና የሚገጣጠሙት የኔትወርክ ዕቃዎች ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸው ተፈትሾና ተረጋግጦ ወደ ተግባር እንዲገባ አድርጓል፡፡

## የበለፀገውን ሶፍትዌር በተመረጡት ማዕከሎች መዘርጋትን (ሲስተሙን ማስፋፋትን) በተመለከተ

84. በፕሮጀክቱ የሚካተቱ (ሲስተሙ የሚስፋፋባቸው) ተቋማትን ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ የማድረግ እንዲሁም የማረጋገጥ ስራ ሊሰራና ወደ ሙሉ ትግበራ ሊገባ ይገባል፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት የሙከራ ትግበራው /ፓይለት ቴስት/ እንደተጠናቀቀ አፈፃፀሙን ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር በጋራ ተገምግሞ ሲስተሙን ማስፋት እንደሚቻል እንደታመናበትና በአፈፃፀም ሂደት የታዩ ጠናካራን ደካማ ጎኖችን እንደግብዓት በመጠቀም በቀጣይ በጀት ዓመታት ሲስተሙ የሚስፋፋባቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት የ2008 እና የ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ የተዘጋጀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ ስለመደረጉና ወደ ትግበራ የገቡ ስለመሆኑ በተደረገው የመስክ ምልከታ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተወሰዱት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ ዝርዝራቸው በአባሪ ከተያያዘ 11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስተቀር የወረዳ ኔት ቢኖራቸውም የሠራተኞችን መረጃ ወደ ተዘጋጀው ሲስተም የማስገባት ስራ ያልተጀመሩ መሆኑ በመስክ ምልከታ ታውቋል፣
- ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉት ዝርዝራቸው በአባሪ ከተያያዘው 24 በክልልና በከተማ አስተዳደር ስር በተለያየ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ

ከባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ሲቨል ሰርቪስ ቢሮ በስተቀር የወረዳ ኔት የተዘረጋላቸው ቢሆንም የሠራተኞችን መረጃ በተዘጋጀው ሲስተም ማስገባት ያልጀመሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

87. ስለ ጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊ  በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የወረዳ ኔት መስመር አገልግሎቱ ለሲስተም ትግበራ ብቻ ሳይሆን ለኢንተርኔት አገልግሎት ጭምር የሚያገለግልና የተሰበሰበውን መረጃ ወደ ሲስተም እንዲገባ ስለሚረዳ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የክልል ፐብሊክ የሰው ሀብት ልማት  ቢሮ ወረዳ ኔት የተዘረጋበት ዋና ዓላማ ማለት በተመረጡ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የሰራተኞችን መረጃ በተዘጋጀው ሶፍትዌር እንዲጠቀሙ፣ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከተፈቀደለት አካል ውጪ /ከደህንነት አንፃር/ የሠራተኞችን መረጃ ጠብቆ ለመያዝ የሚጠቅም መሆኑ፣ የሠራተኞችን መረጃ ከማንዋል አሰራር አላቆ ወደ ዘመናዊ አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ እንጂ ክልሎች ኢንተርኔት እንዲጠቀሙበት ባለመሆኑና የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጹ ከዋናው ማህደር ተሰብስቦ ያላለቀ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ አይደለም፡፡

89. ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉት የክልል ቢሮዎች፣ ዞንና ወረዳ የወረዳኔት አገልግሎትን ለሲስተሙ ስራ እየተጠቀሙ ስለመሆናቸው የማረጋገጥ ስራ ሳያከናውን እና የሰራተኞች መረጃ ወደ ተዘጋጀው ሲስተም ሳይገባ ከ2007-2009 በጀት ዓመት ከፍተኛ ገንዘብ ማለትም ብር 1,813,846.00 የወረዳኔት አገልግሎት ክፍያ ለኢትዮ ቴሌኮም እንዲከፈል አድርጓል፡፡

## ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደርጉ ክልሎች ለፕሮጀክቱ ዓላማ ግብአቶች መዋሉን በተመለከተ

90. ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደርጉ የክልል ሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች ከጽ/ቤቱ የተላኩ አስፈላጊ ግብአቶች /ኮምፒውተሮች፣ ዩ.ፒ.ኤሶች፣ እስካነሮች እና የመሳሰሉት/ ለፕሮጀክቱ  ስራ ብቻ መዋላቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

91. በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ባደረጉ የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮዎች በተደረገው የግብአት ስርጭት ዕቃዎቹ ለፕሮጀክቱ ዓላማ ብቻ ስለመዋላቸው በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በኦዲቱ በናሙና ከታዩት ዝርዝራቸው በአባሪ ከተያያዘ 24 በተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተቋማት ውስጥ ከባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ክልላዊ መንግስት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በስተቀር ከፕሮጀክቱ የተላኩት ግብዓቶች የፕሮጀክቱን ሥራ እንዲሰሩ ስልጠና ካገኙት ባለሙያዎች ውጪ በኃላፊና በፀሐፊ ቢሮ ተቀምጦ ለሌላ የሥራ ዘርፍ ለሚሰሩ ሥራዎች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በመስክ ምልከታና በቃለመጠይቅ ወቅት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶ ዞን ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ፣ ሶዶ ዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ሀዲያ ዞን ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ለፕሮጀክቱ ስራ እንዲሰራባቸው የተሰጡ ኮምፒውተሮቹ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በተቋማቱ ባደረገው የመስክ ምልከታና በቃለመጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለክልሎች የተሰራጩት ግብአቶች ለፕሮጀክቱ ዓላማ ያልዋለ ያለመኖሩን በቃለመጠይቅ ወቅት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

93. የፕሮጀክት ኃላፊው ይህንን ይበሉ እንጂ የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ ኮምፒውተሮቹ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑን፣ ለሌላ የሥራ ዘርፍ ማለትም ለኃላፊዎች፣ ለጽህፈት እና ቢሮ አስተዳደር ፣ ለሰው ኃይል እና ለፋይናንስ ቢሮ እየተጠቀሙባቸው መሆኑን፣ አንዳንዶቹ ከካርቶን ሳይወጡ እንደታሸጉ መቀመጣቸውን፣ ዩፒኤስ እና እስካነር ለምን አገልግሎት እንደሚውል አጠቃቀሙን ባለማወቃቸው የተቀመጡ መሆኑን በአጠቃላይ በመስክ ምልከታው ወቅት ከታዩት ቢሮዎች ግብአቶች ለፕሮጀክቱ ስራ እየተሰራባቸው ያለመሆኑን ለማወቅ የተቻለ በመሆኑ ከኃላፊው የተሰጠው ምላሽ ተአማኒነት የለውም፡፡

94. ስለ ጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከሰው ኃይል አስተዳደር፣ ከሰው ሀብት መረጃ ፣ ከሪከርድና ማህደር ወዘተ ያሉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከላይ ከተዘረዘረሩት የሥራ ሂደቶች ውጭ ለሌላ አገልግሎት እየዋለ ከሆነ አስተያየቱን እንደግብዓት እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

95. ለክልሎች የተሰራጩት ግብአቶች ለፕሮጀክቱ ስራ አለመዋላቸው የሠራተኞች የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አንዳይዘምን/አውቶሜት/ እንዳይሆን ማድረጉ፣ የመረጃ ሃብቱን አደረጃጀትና አጠቃቀም ቀላልና ምቹ እንዳይሆን እንዲሁም የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ቀላልና ቀልጣፋ እንዳይሆን አድርጎል፡፡

## ለሲስተሙ ተጠቃሚዎች በቂ ሥልጠና መስጠትን በተመለከተ፤

### የክልሎች የሚገነቡ የስልጠና ማዕከል ግንባታ በተመለከተ

96. በክልሎች የሚገነቡት የስልጠና ማዕከል ግንባታ ተጠናቆና ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብአቶች እንዲሚሉላቸው ተደርጎ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡

97. በኦዲቱ ወቅት የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ፕሮጀክት የሚጠቀመው ኔትወርክ የመንግሥት የወረዳኔት መስመር በመሆኑ ወደ ክልሎች እየሄዱ ስልጠና ለመስጠት ምቹና የተደራጀ የአይሲቲ ማሰልጠኛ ክፍል /IT Training Lab/ እንደሚያስፈልግ ስለታመነበት በአራቱ ክልሎች /ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ እና ትግራይ/ ካሉ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በመነጋገር የአይሲቲ ማሰልጠኛ እንዲቋቋም ስምምነት ላይ መደረሱን እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብአቶችን እንደሚያሟላ ለማወቅ ተችሏል፡፡

98. በዚህም መሰረት በክልሎች የስልጠና ማዕከል ግንባታ ተጠናቆ ከተሟላ ግብአት ጋር አገልግሎት ስለመስጠታቸው በተደረገው የሰነድ ክለሳ እና የመስክ ምልከታ የሚከተሉትን ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡-

- ✓ በ2008 በጀት ዓመት ለአራቱ ክልሎች /ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ እና ትግራይ/ የአይሲቲ ማሰልጠኛ እንዲቋቋም ለእያንዳዳቸው 25 ኮምፒውተርና 25 ዩ.ፒ.ኤስ ግዥ ተፈጽሞ እንዲወስዱ የተደረገ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

- ✓ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የ2009 በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተከለሰበት ወቅት በአማራ ክልል የስልጠና ማዕከሉ እንደተቋቋመ የተገለፀ ሲሆን፣ ትግራይ እና ደቡብ ብ/ብ ክልሎች በሂደት ላይ መሆናቸውን ነገር ግን በአካል ተገኝቶ ምቹነታቸውን የማረጋገጥ ስራ የተሰራ መሆኑንና ኦሮሚያ ክልል በአጭር ጊዜ ማዕከሎችን እንዲያቋቁም ድጋፍና ክትትል በማድረግ በቀጣይ ማእከሎቹ ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምሩ የተገለፀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. ይሁን እንጂ በኦዲት ቡድኑ በተደረገው የመስክ ምልከታ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮዎች የስልጠና ማዕከላቱ ግንባታ ተጠናቆ ወደ ስራ ያልተገባ በመሆኑ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተላኩት 25 ኮምፒውተሮች እና 25 ዩ.ፒ.ኤሶች ክልሎች የስልጠና ማዕከል ግንባታ በራሳቸው ወጪ አጠናቀው ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብአቶች በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንደሚሟላ በቃል የተላለፈ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በአሁን ወቅት የስልጠና ማዕከሉ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ፣ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ሁለት የስልጠና ክፍል ሲኖራቸው አንዱ ዝግጁ ሲሆን፣ ሁለተኛው ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የሥልጠና ማዕከሉ ተዘጋጅቶ የኔትወርክ ዝርጋታ ያልተጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

101. ስለ ጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በቅርቡ ባደረጉት ክትትልና ድጋፍ የስልጠና ማዕከል ግብአቶች ተሰራጭተው ከትግራይ ክልል በስተቀር ማዕከላቶች ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

102. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ በኦዲት ቡድኑ በታዩት ሶስት ክልሎች ማለትም አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ግንባታው ተጠናቆ ወደ ስራ አለመግባታቸው በመስክ ምልከታ ወቅት በመታየቱ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

103. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱና በክልሎች የስልጠና ማዕከላት ተጠናቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ስልጠናዎችን በመርሃ ግብሩ መሠረት ለመስጠት ካለማስቻሉም በተጨማሪ ከክልል የሚመጡ ሰልጣኞችን ለማስተናገድ አስቸጋሪ እንዲሆንና ከስልጠናው ጋር የተያያዘ አላስፈላጊ ወጪ (ለውሎ አበል፣ ለትራንስፓርት አበል እና ለስልጠና ማዕከል ኪራይ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

## ስልጠና በእቅድ መሰረት መፈፀሙን በተመለከተ

104. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ ለተቋማት ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል እቅድ ሊያዘጋጅና በእቅድ መሰረት ሊፈጽም እንዲሁም ስልጠናው ያመጣውን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡

105. በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስልጠና ለመስጠት እቅድ ማዘጋጀቱና በእቅዱ መሰረት ስለማከናወኑ በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡-

106. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ከታዩት 11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ለ9ኙ በሲስተም እንዴት የሰራተኞች መረጃ ማስገባት እንደሚቻል ስልጠና ቢሰጥም የወረዳ ኔት አገልግሎት የማስተዋወቅ ሥራ ባለመሰራቱ  የሠራተኞችን መረጃ በተዘጋጀው ሶፍትዌር ማስገባት ያልተጀመረ መሆኑን፣ እንዲሁም በኦዲቱ በናሙና ከታዩ ዝርዝራቸው በአባሪ ከተገለጸ በክልልና በከተማ አስተዳደር ስር በተለያየ ደረጃ ላይ ከሚገኙ 24 ተቋማት ውስጥ ከባህርዳር ዙሪያ ወረዳ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በስተቀር ቀሪዎቹ የሠራተኞቹን መረጃ ወደ ተዘጋጀው ሲስተም ሶፍትዌር ማስገባት ያልተጀመሩ መሆኑን በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

107. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የፕሮጀክት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በ2008 በጀት አመት የግንዛቤ ማስጨበጫና የመረጃ ማሰባሰብ ስልጠና ተሰጥቶ በባለሙያ እጥረት ምክንያት የሲስተም አጠቃቀም ስልጠና ከገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስተቀር ለሌሎች ተቋማት ያልተሰጠ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በ2009 በጀት አመት የአጠቃቀም ስልጠና የመስጠትና የማካካስ ሥራ መሰራቱን ገልፀዋል፡፡  ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ላደረጉ የፌዴራል እና የክልል ቢሮዎች የመረጃ ማሰባሰብ፣ ስልጠና ተሰጥቶ ሁሉም ቢሮዎች መረጃ መሰብሰባቸውን ገልጸው ነገር ግን መረጃ ወደ ሲስተም እንዴት

እንደሚገባ የአጠቃቀም ስልጠና ተሰጥቶ ድጋፍና ክትትል ባለመደረጉ በአብዛኛው ሲስተሙን እየተጠቀሙ ያለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ለወደፊት ድጋፍና ክትትል ሲደረግ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

108. ስለ ጉዳዩ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የ2008 በጀት አመት ሁሉም አይነት ስልጠናዎች ኦሪንቴሽን፣ የመረጃ የመሰብሰብና መረጃዎችን ወደ ሲስተም የማስገባት ስልጠና በበጀት አመቱ ባይሰጥም በ2009 በጀት አመት የማካካሻ ስልጠና የሰጡ መሆኑን፣ በፌዴራልና በክልል ተቋማት ሶስት ዙር ስልጠና ቢሰጥም በጽ/ቤቱ የተሟላ የሰው ኃይል ተሟልቶ ድጋፍና ክትትል ባለመደረጉ ተቋማት በተለያዩ ደረጃ ላይ ያሉ መሆኑን፣ በቅርቡ በተደረገው ድጋፍና ክትትል ስራም መረጃ ያልሰበሰቡና መረጃ ወደ ሲስተም ያላስገቡ የክልል ተቋማት መረጃ የመሰብሰብ ስራ አጠናቀው ወደ ሲስተም የማስገባት ስራ እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

109. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስልጠናዎችን በእቅዳቸው መሰረት መከናወናቸውን ባለመገምገሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ኤልክትሮኒክስ ዳታ ቤዝ በማደራጀት እንዳይዘምን፣ በመንግስት ተቋማት የሚከናወኑ የቅጥር የዕድገት፣ የዝውውር እና ተዛማጅ ሂደቶች በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የመጠቀም ሂደቱን ተደራሽ፣ ቀላልና ምቹ እንዳይሆን አድርጎል፡፡

## ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ

110. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲሰተሙን ከሚጠቀሙ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከአጠቃቀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፤ የተቋማቱን አፈጻጸም በመከታተል እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

111. በጽ/ቤቱ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፣ የተቋማቱን አፈፃፀማቸውን በመከታተል እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ስለመደረጉ በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡-

- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፓይለት ሳይቶችን (በ2007 በጀት ዓመት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት ) ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል አነስተኛ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

* በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት አመት ለተካተቱ ሁሉም ተቋማት በአካል እየተገኙ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ትግበራ እንዲገቡ የማድረግ ስራ ያልተሰራ መሆኑ መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
* በኦዲት ቡድኑ በናሙና በታዩት ከ11 የፌዴራል ተቋማት ውስጥ ከገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስተቀር በቀሪዎቹ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣
  * በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በስራ ወቅት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ጥያቄ ቢያቀርቡም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መፍትሄ ያልተሰጠ መሆኑ በቃለመጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣ ፣
  * በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመለየት፣ የተቋማቱን እቅድ አፈጻጸም በመከታተል ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፣

112. ስለ ጉዳዩ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በ2007 በጀት አመት የተመረጡ ፓይለት ተቋማትን በመስክ ተገኝቶ ድጋፍ ማድረጉ፣ በ2008 እና በ2009 በጀት አመት ለፌዴራል ተቋማት ባላቸው ውስን የሰው ኃይል ድጋፍ ያደረጉ መሆኑ፣ ነገር ግን ለክልሎች በወቅቱ ድጋፍ ያልተደረገበት ምክንያት በሰው ኃይል እጥረትና በወቅቱ በነበረው የሀገሪቱ የፀጥታ ሁኔታ መሆኑን፣ የገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ያጋጠሟቸውን ችግሮች እንደፍላጎታቸው በወቅቱ መፍታት አልተቻለም፡፡ ሆኖም በየ15 ቀኑ እየተገናኙ ችግሮቹ መፍትሄ ያገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

113. የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ በ2007 በጀት አመት ለፓይለት ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያለመደረጉን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰነድ ሲከለስ የተገኘ በመሆኑ፣ በ2008 እና 2009 በጀት ድጋፍና ክትትል ስለማድረጋቸው እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጥያቄዎች መፍትሄ ስለማግኘቱ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

114. ፕሮጀክት ጽ/ቤት በየበጀት አመቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ላደረጉት ተቋማት በየወቅቱ ክትትልና ድጋፍ ባለማድረጉ የግብአት ግዥ፣ የስልጠና ወጪና የወረዳኔት

ክፍያ ፕሮጀክቱ ካስገኘው ጥቅም አንፃር ሲታይ ወጪን ያገናዘበ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

## እቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በተመለከተ

115. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፌዴራል ተቋማት እና የክልል መንግስታት የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት የመረጃ ስርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የስራ እቅዳቸውንና የእቅድ አፈጻጸማቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

116. በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 11 የፌዴራል እና 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት እቅዳቸውንና አፈጻጸማቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያቀርቡበት የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በቃለመጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

117. ስለ ጉዳዩ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የመረጃ ስርዓቱን በእቅድ ይዘው አፈፃፀማቸውን ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሪፖርት የሚያደረጉበት ስርዓት ለወደፊቱ ተግባራዊ እንደሚያደረጉ ገልፀዋል፡፡

118. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እቅድና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋና ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ባደረጉ ተቋማት ያልተተገበረ በመሆኑ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የፕሮጀክቱን ስራ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በአግባቡ ለመከታተል ያላስቻላቸው በመሆኑ የኘሮጀክቱ ሥራ እንዲጓተት እና በስራ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች በአፋጣኝ ምላሽ እንዳያገኙ እንዲሁም በክልሎች የኘሮጀክቱ የስራ ባለቤት እና ተጠያቂ አካል ማን እንደሆነ እንዳይታወቅ አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአመታዊ ሪፖርት ግብረመልስ ስለመስጠቱ በተመለከተ

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያቀረበውን ወርሃዊና አመታዊ ሪፖርት ገምግሞ ግብረ መልስ በመስጠት አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

120. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚያቀርበውን ወርሃዊ እና አመታዊ ሪፓርት ገምግሞ ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፡፡

121. ስለጉዳዩ አስመልክቶ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ በየጊዜው ወቅቱን ጠብቆ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ የስድስትና አመታዊ ሪፓርት ቀረቦ ግብረመልስ በሚኒስትሩ ስለመሰጠቱ ገልፀዋል፡፡

122. የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ በተደጋጋሚ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ግብረመልስ ስለመሰጠቱ የሚያስረዳ መረጃ ተጠይቆ መረጃው ሊቀርብ ባለመቻሉ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

123. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ባለመግባቱ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በወቅቱ በመገመገም ትክክለኛ ያለበትን ደረጃ እንዳያውቁ እና ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዳይፈጠር አድረጓል፡፡

## ቋሚ የግንኙነት መድረክ ስለመኖሩ በተመለከተ

124. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበትን ሁኔታ ለመከታተል ቋሚ መድረክ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

125. በኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ 11 የፌዴራል እና 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበት ሁኔታ ለማወቅ ለወደፊትም በምን መንገድ ስራዎችን ማከናወን እንዳለባቸው ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ የሌለ መሆኑን እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደርጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የግንኙነት ጊዜ ስለመኖሩ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፡፡

126. ስለጉዳዩ አስመልክቶ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከክልል ቢሮዎች ጋር በየሩብ አመቱ የምክክር መድረክ የሚያደረጉ መሆኑ፣

የፌዴራል ቢሮዎች  ወደ ሙሉ ትግበራ ባለመግባታቸው በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በአካል የመደገፍ ስራ የተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

127. የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከክልል ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ ስለመኖሩ የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ በተደጋጋሚ እንዲያቀረቡ ቢጠየቁም ምላሽ ባለመስጠታቸው የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም ፡፡

128. ፕሮጀክቱ ወቅቱን ጠብቆ የግንኙነት ጊዜ ባለመኖሩ በስራ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮች በአፋጣኝ ምላሽ ያለመስጠት፣ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት የተሻለ ደረጃ ያሉ ተቋማት የልምድ ልውውጥ ያለማግኘት እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮ እንዳይስፋፉ አድርጎል፡፡

## ክፍል ሶስት

### መደምደሚያ

በሪፖርቱ ክፍል ሁለት ከተዘረዘሩት ችግሮች እና የአሰራር ግድፈቶች በመነሳት በእኛ አስተያየት፣

- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተቀመጠው የመዋቅር/ አደረጃጀት ጥናት/ መሰረት ስራውን የሚደግፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ፣ ጽ/ቤቱ የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት ተግባራዊ ላደረጉ ለፌዴራልና ለክልል ተቋማት የአፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ ያላሰራጨ መሆኑ እንዲሁም ጽ/ቤቱ የስልጠና ማንዋሎችን በክልሉ የስራ ቋንቋ ማለትም /በኦሮምኛ እና በትግሪኛ/ ተተርጎሞ ለተገልጋይ ተደራሽ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕሮጀክቱ የመረጃ ማዕከል እቃ ግዥ፣ የማዕከሉን ግንባታና የማማከር ስራ በግዥ መመሪያ መሰረት ያልተከናወነ መሆኑ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የዳታ ማዕከሉ ግንባታ እና የማማከር ሥራ ለመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ያለጨረታ የተሰጠ መሆኑ፣ መረጃ ማዕከል በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በ4 የክልል ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮዎች ግንባታው ተጠናቆ ሥራ ያልተጀመረ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ የሚያስፈልጉ የኔትወርክ ዕቃዎች ግዥቸው ተፈጽሞ በውሉ ላይ አቀርባለሁ ብለው በተወዳደሩበትና ባሸነፉበት ዝርዝር መግለጫ /specification/ መሰረት መሆኑን አረጋግጦ ርክክቡን ያልተከናወነ መሆኑ፣ የሶፍትዌር ማልማት፣ የኢንፍራስትራክቸር እና የዳታ ማዕከሉን ግንባታ የግብአት ግዢ በውሉ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ክትትልና ቁጥጥር በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በፕሮጀክቱ የሚካተቱ (ሲስተሙ የሚስፋፋባቸው) ተቋማትን ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ የማድረግ እንዲሁም የማረጋገጥ ስራ ያልተሰራና ወደ ሙሉ ትግበራ ያልተገባ መሆኑ፣ በአዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ዝርዝራቸው በአባሪ የተያያዘ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ 24 ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የክልል ተቋማት ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተላኩ አስፈላጊ ግብአቶች/ ኮምፒተር ፣ ዩፒየስ ፣ እስካነር/

የመሳሰሉት ከ2 ማለትም ከደቡብ ብሄረ ብሄረሰብ ክልላዊ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እና ከባህርዳርዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት በስተቀር ለፕሮጀክቱ የተላኩ ግብአቶች የፕሮጀክቱን ስራ ለማከናወን /የሠራተኞችን መረጃ ወደ ተዘጋጀው ሶፍትዌር ለማስገባት/ አገልግሎት ያልዋሉ መሆኑ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በክልሎች የሚገነቡት የስልጠና ማዕከል ግንባታ ባለመጠናቀቁ የተላኩ ግብአቶችን አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ ለተቋማት ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል እቅድ ያዘጋጅ ቢሆንም አፈጻጸሙ በዕቅድ አፈጻጸም ላይ ያልተገለጸ መሆኑ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲስተሙን ከሚጠቀሙ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ከአጠቃቀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፤ የተቋማቱን አፈፃፀም በመከታተል እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፣ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደረጉ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት እቅዳቸውንና አፈጻጸማቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያቀርቡበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚያቀርበውን ወርሃዊና አመታዊ አፈፃፀም ገምግሞ ግብረ መልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ባደረጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበትን ሁኔታ ለመከታተል ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ የሌለ መሆኑ፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች በመኖራቸው ፕሮጀክቱ የተነሳበትን ኃላማ ማለትም የሰራተኞች የመረጃ አያያዝ ስርዓት ከማንዋል አሰራር ወደ ኤሌክትሮኒክስ ስርዓት እንዳይዘምን አድረጓታል፡፡

129. በአጠቃላይ በኦዲቱ እንደተገነዘብነው የተቀናጀ የሠራተኖች መረጃ አያያዝ ፕሮጀክት አፈጻጸም ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ ለክልሎች ማሰራጨት፣ የስልጠና ማንዋሉን በክልል የስራ ቋንቋ መተርጎም፣ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራ መግባት፣ የዳታ ማዕከል ግንባታው በተዋዋለበት ውል መሠረት ማከናወን፣ ንብረቶችን በዝርዝር መግለጫው መሠረት ገቢ ማድረግ፣ የተሰጡት ግብዓቶች ለፕሮጀክቱ ሥራ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣ ወረዳ ኔቱ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣ እንዲተረጎም ማድረግ እንደሚገባ ተረድተናል፡፡ስለሆነም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚታዩ የአሰራር ግድፈቶች መፍትሄ የማይሰጥ ከሆነ በአገር አቀፍ

የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ከማንዋል አሰራር የማይላቀቅበት ሁኔታ ይከሰታል ብሎ ያምናል፡፡ከላይ የተገለጹትን በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ የታዩትን ግድፈቶችን ለማስወገድ ወይም ለማስተካከል ይረዳል ብለን ያሰብናቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ

- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተቀመጠለት የመዋቅር አደረጃጀት ጥናት/ መሰረት ስራውን የሚደግፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ስራው ሊገባና ፕሮጀክቱ የሚያጋጥመውን ችግር በቅርበት ሊከታተልና ሊፈታ ይገባል፣
- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ላደረጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ሊያሰራጭ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስልጠና ከመስጠቱ የግብዓት ስርጭት ከማድረጉ በፊት የስልጠና ማንዋሎችን በክልሉ የስራ ቋንቋ ማለትም /በኦሮምኛ እና በትግሪኛ/ መሰረት ተደረጎ ለተገልጋዮች ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ለማድረግ የመረጃ ማዕከል እቃ ግዥ፣ የማዕከሉን ግንባታና የማማከር ስራ መንግስት ባዘጋጀው የግዢ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆንበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፣
- ✓ የመረጃ ማዕከሉን ግንባታ አማካሪ ድርጅት ግንባታውን ከሚፈፀመው አካል ውጪ በገለልተኛ አካል የማማከር ስራ ሊሰራ ይገባል፣
- ✓ በፌዴራል እና በክልል ቢሮዎች የሚገነባው የዳታ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ የሚያስፈልጉ የኔትወርክ ዕቃዎች ግዥቸው ተፈጽሞ በውሉ ላይ አቀርባለሁ ብለው በተወዳደሩበትና ባሸነፉበት ዝርዝር መግለጫ /specification/ መሰረት በተገቢው ባለሙያ ተመሳክሮ ገቢ ሊያደረግ ይገባል፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሶፍትዌር ማልማት፣ የኢንፍራስትራክቸር እና የዳታ ማዕከሉን ግንባታ የግብአት ግዢ በውሉ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፣
- ✓ በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ተቋማትን ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ የማድረግ እንዲሁም የወረዳ ኔት ያገኙትን ክልሎች በአገልግሎቱ ስለመጠቀማቸው የሚያረጋግጥበት የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፣

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደረጉ የክልል ሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተላኩ አስፈላጊ ግብአቶች/ ኮምፒተር፣ ዩፒኤስ ፣ እስካነር/ የመሳሰሉት ለፕሮጀክቱ ስራ መዋሉን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በክልሎች የሚገነቡት የስልጠና ማዕከል ግንባታ ተጠናቆ ከፌዴራል የተላኩ ግብአቶች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ካደረጉ መ/ቤቶች በየበጀት ዓመቱ የስልጠና ፍላጎት መግለጫ በማሰባሰብ ለፕሮጀክቱ ሥራ ቅርበት ያለው ሰልጣኝ እንዲሰለጥን የሚያስችለውን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ ለተቋማት ስልጠና ለመስጠት የሚያሰችል እቅድ ሊያዘጋጅ እና ባቀደው መሠረት ስለመከናወኑ በአፈፃፀም ሪፓርት ላይ በግልፅ ሊያሳይና እንዲሁም ስልጠናው ያመጣው ውጤት የሚገመገምበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲሰተሙን ከሚጠቀሙ ከሁሉም የፌዴራልና የክልል ተቋማት እንዲሁም በዞንና ወረዳ ከአጠቃቀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፤ የተቋማቱን አፈጻጸም በመከታተል እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፌዴራል ተቋማት እና የክልል መንግስታት የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት የመረጃ ስርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የስራ እቅዳቸውንና አፈጻጸማቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚያቀርበውን ወርሃዊና አመታዊ ሪፖርት ገምግሞ ግብረ መልስ በመስጠት አፈጻጸሙን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፣
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበትን ሁኔታ ለመከታተል ቋሚ መድረክ /የግንኙነት ጊዜ/ ወቅቱን የጠበቀ ማለትም በየሩብ ፣ በስድስት፣ በዘጠኝ ወር እና በአመት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፣

130. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የፌዴራል ተቋማት፣ የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፣ ክፍለ ከተማ፣ ዞንና ወረዳ ፐብሊክና ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፍርት( Evaluative Criteria)

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ፡- የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር

| የኦዲት ጭብጥ (issue | የመገምገሚያ መስፈርት/ Evaluative Criterial) |
|---|---|
| 1. ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል የሚከናወኑ የንብረት እና የአገልግሎት ግዥዎች በመንግስት ግዥ መመሪያ መፈፀሙን፣ የተገዙ ንብረቶችም ለፕሮጀክቱ ኃላማ መዋሉን ለፕሮጀክት አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፣ | 1.1. የዳታ ማዕከሉን እቃ ግዥ፣ የማዕከሉን ግንባታና የማማከር ስራ የመንግስትን የግዥ መመሪያ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፣ |
| | 1.2. የኔትወርክ ዝርጋታ እና የዳታ ማዕከሉን ግንባታ የግብአት ግዢ በውሉ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ስራዎችን ተፈፀሚ እያደረገ ስለመሆኑ መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፣ |
| | 1.3. ተጫራቾች የሚያቀርቧቸውን እቃዎች በውሉ ላይ አቀርባለሁ ብለው በተወዳደሩበትና ባሸነፉበት ዝርዝር መግለጫ /specification/ መሰረት መሆኑን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፣ |
| | 1.4. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደረጉ የክልል ሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች ከጽ/ቤቱ የተላኩ አስፈላጊ ግብአቶች/ ኮምፒተር ፣ ዩፒየስ ፤ እስካነር/ የመሳሰሉት ለፕሮጀክቱ ስራ መዋላቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.5 በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ተቋማትን ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ የማድረግ እንዲሁም የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፣ |
| | 1.6 በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ተቋማትን ከወረዳኔት መስመር ጋር እንዲገናኙ የማድረግ እንዲሁም የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፣ |

| | |
|---|---|
| | 1.7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዳታ ማዕከሉ ግንባታ አማካሪ ድርጅት ሊኖረው ይገባል፣ |
| | 1.8 ፕሮጀክት ጽ/ቤት በፌዴራልና በክልል ሲቨል ሰርቪስ ቢሮ የአፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ ሊያሰራጭ ይገባል፣ |
| 2. ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለሚያደረጉ የፌዴራልና የክልል አገልግሎት ስጪ ተቋማት በጽ/ቤቱ ስለሚዘረጋው ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት አጠቃቀም በተመለከተ የሚደረግላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ፣ የትምህርትና ስልጠና እንዲሁም በስራው ወቅት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የሚደረግላቸውን ድጋፍና ክትትል ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | 2.1 የመረጃ ማዕከል/data base/ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በ4 ክልሎች ሲቨል ሰርቪስ ቢሮዎች ግንባታው ተጠናቆ ወደ ስራ መግባት አለበት፡፡ |
| | 2.2. ፕሮጀክቱ የሚጠቀመውን የአሰራር ስርዓት በአግባቡ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችል  የአይቲ ባለሙያ ሊያሟላው የሚገባውን መስፈርትሊዘጋጅ እና በሁሉም የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት በመሰፈርቱ መሰረት  ባለሙያ ሊመድቡ እና ቅጥር ሊፈጽሙ ይገባል፡፡ |
| | 2.3 በክልሎች የሚገነቡት የስልጠና ማዕከል ግንባታ አስፈላጊ ግብአቶች ተሟልተው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፣ |
| | 2.4. ኘሮጀክት ጽ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ ለተቋማት ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል እቅድ ሊያዘጋጅና በእቅድ መሰረት ሊፈጽም እንዲሁም ስልጠናው ያመጣውን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 2.5. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲሰተሙን ከሚጠቀሙ የፌዴራልና የክልል ተቋማት  ከአጠቃቀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፤ የተቋማቱን አፈጻጸም በመከታተል እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ  ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.6 ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የስልጠና ማንዋሎችን ተግባራዊ በሚደረግባቸው የክልል የስራ ቋንቋ መሰረት ተደረጎ ለተገልጋይ ተደራሽ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 2.7 ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፌደራል ተቋማት እና የክልል መንግስታት የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ማኔጅመንት የመረጃ ስርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የስራ እቅዳቸውንና የእቅድ አፈጻጸማቸውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 3. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆነው ስራ ተፈፃሚ ለማድረግ እንዲያስችለው ከባለድርሻ አካላት ( ኢትዮ ቴሌኮም፣ የመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር እና የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ) እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለሚያከናውናቸው ስራዎች የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት የተጠናከረና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | 3.1 ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተቀመጠለት መዋቅር / አደረጃጀት ጥናት/ መሰረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከውስጥና ከውጪ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል<br><br>3.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚያቀረበውን ወርሃዊና አመታዊ ሪፓርት ገምግሞ ግብረ መልስ በመስጠት አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br><br>3.3 ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደረጉ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ፕሮጀክቱ ያለበትን ሁኔታ ለመከታተል ቋሚ መድረክ / የግንኙነት ጊዜ/ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፣ |

## አባሪ 2

**በናሙና የተመረጡ የፌዴራልና የክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በአካል በመሄድ መረጃ የተሰበሰበባቸው**

| ተ.ቁ | የፌዴራል ተቋማት፣ ክፍለ ከተማ እና የክልል ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ | ክልል |
|---|---|---|
| 1. | ትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 2. | ከተማ ልማት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 3. | ንግድ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 4. | ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 5. | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 6. | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 7. | የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 8. | ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 9. | ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 10. | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 11. | የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲዩት | አዲስ አበባ |
| 12. | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 13. | አራዳ ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 14. | የካ ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 15. | ቦሌ ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 16. | አማራ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ባህርዳር |
| 17. | ደብርማርቆስ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ደብርማርቆስ |
| 18. | ደብርማርቆስ ከተማ አስተዳደር የዞን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ | ደብርማርቆስ |
| 19. | ደብርማርቆስ ከተማ አስተዳደር ማቸከል ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ደብርማርቆስ |
| 20. | ደብርማርቆስ ከተማ አስተዳደር ጎዞመን ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ደብርማርቆስ |
| 21. | ፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ፍኖተሰላም |
| 22. | ፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር የዞን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ | ፍኖተሰላም |
| 23. | ፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር ጃቢጠና ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ፍኖተሰላም |
| 24. | ባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ባህርዳር |
| 25. | ደቡብ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሀዋሳ |
| 26. | ሶዶ ከተማ አስተዳደር የዞን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ | ሶዶ |
| 27. | መስቃይ ወረዳ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | |
| 28. | ሶዶ ከተማ አስተዳደር ሶዶ ዙሪያ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው | ሶዶ |

| | | |
|---|---|---|
| | ሀብት ልማት ጽ/ቤት | |
| 29. | ሀዲያ ከተማ አስተዳደር የዞን ሲቭል ሰርቪስ መምሪያ | ሆሳህና |
| 30. | ሀዲያ ከተማ አስተዳደር ሌሞ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ሆሳህና |
| 31. | የሲዳማ የዞን ሲቭል ሰርቪስ መምሪያ | ሀዋሳ |
| 32. | የሲዳማ ዞን የሺበዲኖወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ሀዋሳ 26 ኪሎ ሜትር |
| 33. | የኦሮሚያ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 34. | ሰሜን ሸዋ ዞን ሲቭል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ | ፍቼ |
| 35. | ሰሜን ሸዋ ዞን ግራር ጃርሶ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት | ፍቼ |

## አባሪ 3.

### የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የስራ ሂደት መግለጫ

ፕሮጀክቱን ተግባራዊ የሚያደረጉ የክልል ቢሮዎች በመመዘኛው መስፍርት መሰረት ለክልሉ መንግስታት መረጠው እንዲልኩ ማሳወቅ፣ የፌዴራል ተቋማትን በመምረጫ መስፈርት መሰርት ፕሮፖዛል ለከፍተኛ አመራሩ ቀርቦ በማጸደቅ ወደ

↓

ከወረዳ ኔት ጋር ያልተገናኙ ተቋማትን ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶች (መገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር እና ኢትዮ ቴሌኮም) ጋር በመተባበር በወረዳ ኔት ጋር እንዲተሳሰሩ ይደረጋል

↓

የወረዳ ኔት ጋር የተገናኙ ተቋማትን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ወደ ሲስተሙ እንዲገቡ የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፣ በተመረጡ ተቋማት ላይ ለፕሮጀክት ስራው አሰፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን

↓

የተሰበሰበው መረጃ ወደ ተዘረጋው የመረጃ አያያዝ ስርዓት ውስጥ እንዴት እንደሚገባ እና የሲስተም አጠቃቀም ስልጠናዎች በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ይሰጣል፤ ተቋማቱን ከመ/ኢ/ሚኒስቴርና ከኢትዮ

↓

በተሰጣቸው አድራሻ መሰረት ተቋማቱ የሰበሰቡትን የሰራተኞች መረጃ ወደ ሲሰተሙ ያስገባሉ፡፡